"ሳፊር ናማህ" በተሰኘው መዕሃፉ ናሲር ኻስሩ ሊባኖሳዊዋ ከተማ ትሪፖሊ በሰላሐዲን ጊዜ ምን ትመስል እንደነበር ሲገልፅ እንዲህ ይላል፦

> የተለያዩ እርሻዎች፣ የሸንኮራ አገዳ፣ የመንደሪን፣ የሙዝ፣ የብርቱካን እና የሎሚ አትክልቶች ዙሪያዋን የከበቧት ውብ ከተማ ናት። መንገዷቿ እና የገበያ ሥፍራዎቿ እጅግ በጣም ንፁህ እና ውብ ናቸው። እያንዳንዱ የገበያ ቦታ የተሸቶጠቶጠ ቤተ መንግስት ይመስላል ብለህ እንድታስብ ያደርግሃል። በከተማዋ አምብርት ላይ ግዙፍ እና ያጌጠ መስጅድ አለ። በመስጅዱ ቅኖር ግቢ ውስጥ የመስጅድ ቁባ የሚመስል ውስጡ አምነበረድ የተነጠፈበት የውሃ ማጠራቀሚያ ታንክር ይገኛል። ከግቢው መሐል ላይ ከቢጫ ኮፖር የተሰራ ፏፏቴ ይታያል። በገበያ ቦታዎችም እንዲሁ አምስት ቢንቢ ያላቸው የህዝቡን የመጠጥ ውሃ የማግኘት ፍላጎት የሚያረኩ የውሃ ታንክሮች አሉ። አንድ ትልቅ የወረቀት ማምረቻ ፋብሪካ አለ። ነገር ግን ከተማዋ ተወርራ በነበረበት ጊዜ ሁለመናዋ ወድሞ ነበር። ህዝቦቿ በየቦታው ይገደሉ ነበር። ቤተ-መፅሐፍቷ ተቃጥሎ፣ ትምህርት ቤቶቿ ፈርሰው፣ የወረቀት ፋብሪካዋም ወደ አመድነት ተቀይሮ ነበር።

ሰላሐዲን ከተማዎችን በመገንባት እና የንግድ ሥርዓቱን እና እንቅስቃሴውን በማሳደግ በኩል ትልቅ ሚና እንደነበረው ለመረዳት እስካሁን ያየነው ብቻ ይበቃናል። የናስር ኻስሩን ምስክርነት በማየትም ትሪፖሊ ውስጥ የወረቀት ፋብሪካ ነበር ብለን መደምደም እንችላለን። ይህ ከሰላሐዲን ስኬቶች ውስጥ አንዱ ነበር። የወረቀት ኢንዱስትሪው ወደ አውሮፓ የተሻገረው በመስቀል ወራሪዎች አማካኝነት ሲሆን አውሮፓ በዚህ ሁኔታ ከወረቀት ኢንዱስትሪ ጋር ከተዋወቀች በኋላ የመጀመሪያው ፋብሪካዋ የተቋቋመው እ.ኤ.አ በ1189 ቤልጅየም ውስጥ ነበር። እንግለዝ እስከ አስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ምንም ዓይነት የወረቀት ኢንዱስትሪ አልነበራትም።

የሰላሐዲንን ትኩረት ካገኙ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች መካከል፦ የጦር መሳሪያ፣ የጨርቃ ጨርቅ፣ የሽመና ሥራ፣ በተለይ የሐር ክሮችን

ተጠቅመው በተለየ ዲዛይን የሚሰሩ ልብሶች እና የፈረስ ኮርቻ የሚያመርቱ ኢንዱስትሪዎች ይገኙበት ነበር። የሸክላ ሥራ እና የመርከብ ሥራም እንዲሁ በዘመኑ ትልቅ ደረጃ ላይ ደርሰው ነበር። ኢኮኖሚውን ያሳደጉ እና ምርቱን የጨመሩ ሌሎች ኢንዱስትሪዎች እንደነበሩ ይታወቃል።

ማሕበራዊ ተሐድሶ

በሰላሑዲን ዘመን ቁም ነገረኝነት፣ ፍራንኮችን መቃወምና ከጠላቶች ጋር መታገል ማህበራዊ ሕይወት ተለይቶ የሚታወቅባቸው ነገሮች ነበሩ። ጉረኝነት፣ ኩራት እና የተጋነነ የጊዜና የገንዘብ ብክነት ምልክታቸው እንኳ የማይታይበት ጊዜ ነበር።

ተራ ልብሶችን በመልበስ፣ ተራ ምግቦችን በመመገብ፣ በትህትና በመራመድና በመቀመጥ፣ በአጠቃላይ ቀላል ሕይወት በመምራት ሰላሑዲን ለወታደሮችም ይሁን ለተራ ዜጎች ዓርአያ ነበር። አል-ዓማድ አል-አስፈሃኒ የሳላሃዲንን አለባበስ እና ማህበራዊ ሕይወት አስመልክቶ ሲገልፅ እንዲህ ብሏል፡- "ከላይነን፣ ከጥጥ እና ከሱፍ የተሰሩና የተፈቀዱ (ሐላል) ልብሶችን ይለብስ ነበር። የንጉስነት ስሜት ምንም ሳይሰማው ከተራ ሰዎች ጎን ይቀመጥ ነበር።"

ሰላሑዲን የፈረስ ግልቢያ እና የኳስ ጨዋታ የሚያዘወትር ስፖርተኛ ነበር። ሌሎች ሰዎችንም ስፖርት እንዲሰሩ ያበረታታ ነበር። ከዙህር ሶላት በኋላ የፖሎ ጨዋታ ውድድር ወደሚደረግበት ሜዳ ፈረስ እየጋለበ ሔዶ እስከ ዓስር ድረስ ጨዋታውን ይመለከትና ያበረታታ ነበር። እሱ ራሱ ከአጃቢዎቹ እና ከጓደኞቹ ጋር ይጫወት ነበር። አደን በህዝቡ ዘንድ በጣም ተወዳጅ መዝናኛ ነበር። ብዙ ጊዜ ሰዎች በቡድን ወይም ብቻቸውን ሁነው በመውጣት ወፎችን፣ ጥንቸሎችን እና ሌሎች እንስሳት ያድኑ ነበር፣ ዓሳ በማጥመድ ይዝናኑ ነበር።

ይህ ዕውነታ ሰላሑዲን ጠላቶቹን በጀግንነት ለመጋፈጥ የነበረውን ዝግጅት መጠን ያሳያል። የፋጢሚዮች ዘመን በተለይም ናይሩዝን በመሳሰሉ የግብዣ እና የክብረ በዓል ቀናት ገንነው ይታዩ የነበሩ የውርደትና የዝቅጠት ገፅታዎችን ጠራርጎ ማጥፋት መቻሉ በማህበረሰቡ

ውስጥ ካሳካቸው ትሳልቅ የተሐድሶ ተግባራት ውስጥ የሚጠቀስ ነበር። የግብፅ ህዝብ የነበረበትን የዝቅጠት ደረጃ ማወቅ ከፈለግን "አል-ኹጡጥ" በተሰኘው መፅሃፉ አል-መቅሪዚ ያስቀመጠውን እንመልከት።

> በናይሩዝ በዓል ጊዜ ከፉ ድርጊቶች ይብረከቱ ነበር። መጥፎ ነገሮች በግልፅ ይፈፀሙ ነበር። በዚህ ቀን የናይሩዝ ልዑል በሚል መጠሪያ የሚታወቅ ሰው በፈረስ ላይ ተቀምጦ እየተዘዋወረ ለደሃዎች የማይሆን ግብር እንዲከፍሉ ሐብታሞችን ይጠይቅና በትንሽ ስጦታ ተሸንግሎ ይመለስ ነበር። ምግባረ ብልሹ የሆኑ ሴቶች እና ወንዶች "ልዑል ቤተመንግስት" ውስጥ ከኹለፋው ፊት ተቀላቅለው ይታይሙ ነበር። ድምፆች ከፍ ይላሉ፤ ወይን በየመንገዱ ይጠጣል፤ ሰዎች እርስ በርሳቸው በውሃ እና በወይን ወይም በቆሻሻ ውሃ ይረጫጫሉ ነበር። በዚህ ቀን አንድ መልካም ሰው ሰራሱ ጉዳይ ከቤቱ ከወጣ በቆሻሻ ውሃ በስብሶ እና ቆሽሾ ይመለስ ነበር።

ሰላሑዲን ለዚህ ሁሉ ማብቂያ አደረገለት። ህዝቡ ከምግባረ ብልሹነት ተላቅቆ፤ ባደባባይ ከሚፈፀሙ አስነዋሪ ነገሮች ርቆ፤ ንፁህና ሀአዳ ሕያውት እንዲመራ አደረገው፤ የኢስላምን ክብር መርሆዎች እና አስተምህሮዎች ለመከተል አበቃው።

ሰንይማኖታዊ ፌጠራዎችም እንዲሁ መቋጫ አድርጎላቸው ነበር። ለምሳሌ የዓሹራ ቀን (የመሐረም ወር አሥረኛ ቀን) ህዝቡ በሃዘን እና በለቅሶ የሚያሳልፈው ቀን ነበር። ሥራ ቁሞ፤ የንግድ ቦታዎች ተዘግተው፤ እያንዳንዱ ሰው ልክ በጣም የሚወደውን ሰው በሞት የተነጠቀ ይመስል አገሮና ተረብሾ የሚያሳልፈው ቀን ነበር። ሳላሃዲን እነዚህን መጥፎ ልማዶች እና የትኖፊት ፌጠራዎች (ቢድዓ) አስወገዳቸው። ዓሹራን የሐዘንና የትካዜ ቀን መሆኑን አስቀርቶ፤ የፈንጠዚያ፤ የደስታ እና የልግስና ወይም የሶደቃ ቀን አደረገው። እንዳለፉት ጊዜያት ሳይሆን፤ ሰዎች አዳዲስ ልብሶችን ለብሰው፤ ከረሜላ እና ሌሎች ጣፋጭ ምግቦችን አዘጋጅተው እየተጫወቱና እየተጠያየቁ የሚያስቡት ቀን ሆነ ዓሹራ። ያለምንም ጥርጥር የሳላሃዲን ተግባሮች ከኢስላም መርሆዎችና አስተምህሮዎች ጋር የሚጣጣሙ ነበሩ

ምክንያቱም ከሌሎች ተራ ቀኖች በተለየ ቤተሰብን ዘና በማድረግ የዓሸራ ቀንን አስቦ መዋል ነቢያዊ ሱና ነውና።

ከሰላሑዲን ስኬቶች ውስጥ አንዱ የህዝቡን ሸክም አክብደውት የኖሩትን በርካታ የግብር ዓይነቶች ማስተረቱ ነበር። ለምሳሌ የሐጅ ተጓዦች የድንን ከተማ ከመርገጣቸው በፊት እንዲከፍሉ በመነው ልዑል ተነሰፋቸው የነበረው የግብር ዓይነት እንዲሰረዝ አድርጎ በምትክ ለልዑሉ 672 ኪሎ ግራም ስንዴ ይልክለት ነበር። ይሁን እንጂ ስንዴው ለመነ ነዋሪዎች እንዲደርስ የሚያስንድድ መስፈርት አስቀምጦ ነበር ማክሸፉን የሚሰጠው። በዚህ መልኩ ከመነ ተጓዦች ላይ የተጫነውን ሸክም አቅልሉ የመነ ነዋሪዎችንም ይደግፍ ነበር።

ሰላሑዲን መልካም አሳቢና ቅን ሰው ስለነበር፤ በህበረተሰቡ ውስጥ ሠላምን ለማስፈን፤ ለሙስሊሞች አንድነት እና ኢፍትሃዊነትን ለማስወገድ ያለመታከት ይሠራ ነበር። የአሊያ ገቨር ሁኖ ለተሾመው ልጁ የሰጠው ምክር ይህን የመልካም አሳቢነት እና የቅንነት ስሜቱን ያሳያል። በኢብን ሸዳድ ዘገባ መሠረት ለልጁ የሰገሰው ምክር የሚከተለው ነበር፦

> አላህን መፍራት የመልካም ነገሮች ሁሉ ቁልፍ ነውና አላህን እንድትፈራ፤ የመጻኛ ጎዳና ነውና የአላህን ትዕዛዝ እንድታስከብር እንዲሁም የጦርነት አሳት አንድ ጊዜ ከተለኮሰ ማቆሚያ የለውምና ጦርነት ውስጥ ለመግባት እንዳትቸኩል አመክርሃለሁ። የህዝቦችን ጉዳይ እንድትከታተል እና እንድትጠብቅ አደራ አልሃለሁ፤ አላህ አደራ የጣለብህ ጠባቂያቸው ነህና። የምታልመውን ለማሳካት ያረዳሃልና ከልዑላን እና መኳንንቶች ጋር ያለህን ግንኙነት አሳምረህ እንድትጠብቅ አመክርሃለሁ። ሁሉንም የሚያዳርስ ሞት አለና በማንም ላይ ቂም አትያዝ። የሁሉንም ሰው መብቶች በእኩልነት እና በፍትህ ጠብቅ፤ ምክንያቱም አንተ በአነሱ ላይ ፍትህ ካጎደልክ፤ የአነሱን ይቅርታ አስነሳገኘህ ድረስ የአላህን ይቅርታ አታገኝም። የአላህን መብት ባትጠብቅ ግን ከልብህ ተፀፅተህ ይቅርታውን እስከለመንክው ድረስ አላህ መሐሪ እና ይቅር ባይ ነውና ይቅር ይልሃል።

ሲጠቃለል፣ ሰላሑዲን ለማህበራዊ ተሐድሶ እና ለሞራል መጎልበት ትልቅ ትኩረት ይሰጥ ስለነበር መልካም ባህሪያት እና ልማዶች በሙስሊሙ ማህበረሰብ ውስጥ ገዥ ባህሪዎች መሆን ችለው ነበር።

ሐይማኖታዊ ተሐድሶ

ከዚህ በፊት እንደጠቀስነው፣ ሰላሑዲን በኢማኑ፣ በዒባዳው፣ ለአላህ በነበረው ፍራቻ፣ በእሱ ላይ በነበረው ፍፁም መመካት እና ፍፁም የሆነ መጠለል ተለይቶ ይታወቅ ነበር። "ከልቡ አማኝ ነበር። የአላህን ስም አብዝቶ ያወሳ ነበር። ዕምነት እና አመለካከቱ ከትላልቅ መሻይኾች እና ምሁራን የተቀዱ ነበሩ።" በማለት ሰላሑዲን ተኮትኩቶ ያደገበትን እና የኖረበትን የዕውቀት እና የዕውነት ከባቢ አየር አል-ቃዲ ቤሐኡዲን ለመግለፅ ሞክሯል። በእንዲህ ዓይነት አየር ውስጥ ያደገና የኖረ ሰው ዝሙትን በመዋጋት፣ የሥነ-ምግባር አፈንጋጭነትን በማስተካከል፣ የኩፍርን ጨለማ በመግፈፍ እና ወደ ኢስላም መርሆዎችና አስተምህሮዎች በመጋበዝ ኃይማኖታዊ ተሐድሶ ለማምጣት ጥረት ማድረጉ የሚጠበቅ እንጂ የሚገርም አይሆንም።

ሰላሑዲን ቅን ልቡን እና ዕኑ ዕምነቱን ይዞ የቢድዓን ቀንበር መስበር ጀመረ፣ የክህደት አስተሳሰቦችን እና ልማዶችን ከሥራቸው ለመንቀል ታገለ። ምሁራኑን እና የህግ ሊቆችን ካማከረ በኋላ በሁሉም የሙስሊም አገሮች ውስጥ የሚገኙ ቢድዓ መሥራቾችን እና ከኢስላማዊው ህግ ጋር ወደ ሚጋጨ መርሆዎች እና መመሪያዎች ጥሪ የሚያደርጉ ጠማሞችን በሙሉ መከረ፣ አስመከረ። እምቢ ብለው በጥመታቸው የፀኑትን አስወገደ። አል-ቃዲ ቤሐኡዲን እንዲህ በማለት ይገልፀዋል፡-

ምንጊዜም ለኃይማኖታዊ ሥርዓቶች ትልቅ ክብር ነበረው። ፈላስፋዎችን፣ በኃይማኖታዊ ጉዳይ ላይ አዲስ ነገር ፈጣሪ የሆነውን የሙዓጢል ቡድን እና ከኢስላም ህግ አፈንጋጮችን አይወዳቸውም ነበር። በግዛቱ ውስጥ አፈንጋጭ የቢድዓ ሰው መኖሩን ከሰማ እንዲገደል ትዕዛዝ ያስተላልፍ ነበር።

ለፋጢሚያ ሸሊፋ ለአል-ዓዲድ የበላይ አስተዳዳሪ ሆኖ በሚያገለግልበት ጊዜ፣ ከነቢዩ (የአላህ ሰላምና ዐጋ በእርሳቸው ላይ ይሁን) እና ከሶሃባዎቻው መንገድ ጋር ፍፁም የማይስማሙና የተላመሙ ዕምነቶች እና ከነሁሁ ጎዳና ያፈነገጡ ቡድኖች የግብፅን ህዝብ ተቆጣጥረውት የተመለከተ ጊዜ ከልቡ ያዘነ ነበር። ምሳሌ መጥቀስ ካስፈለገ እነዚህ ቡድኖች ስለ ኢማምነት (መሪነት) የነበራቸውን ዕምነት ማንሳቱ ያዚቃል። እንደነሱ ዕምነት፣ ኢማምነት በህዝቡ እጅ አይደለም። ህዝቡ ኢማሞቹን የመምረጥ መብት የለውም። ምክንያቱ ደግሞ ኢማሞች የጎደማኖት እንድ ምሰሶ ናቸው። ነቢዩም ቢሆኑ ኢማሞችን የመምረጥን መብት ለህዝቡ አሳልፈው ለመስጠት የሚያስችል ፍቃድ አልነበራቸውም። ስለዚህ መልዕክተኛው ከማለፋቸው በፊት ኢማም መምረጥ ነበረባቸው። የሚመረጠው ኢማም ደግሞ ፍፁም የማይሳሳት እና ንፁሂያት የለሽ መሆን ነበረበት። ነቢዩ ዓለ ኢብን አቢ ጧሊብን ከላቸው በኋላ ሙስሊሙን ዑማ የሚመሩ ዒማም አድርገው መርጠዋቸው ነበር ነገር ግን አብዛኛው እና ዑመር ኢማምነቱን ነጠቂቸው በማለት የፊጠራ ታሪካቸውና ስህተታቸው ሥር እንዲሰድ አድርገው ነበር። ከዚህም በላይ ጥምመት የጠናባቸው ደግሞ ኢማሞች መለኮታዊ ባህሪያት የተላበሱ ልዩ ሰዎች ወይም እምላክ የሰረፀባቸው ሰዎች ናቸው ብለው እስከማመን ደርሰው ነበር። ሌሎች ደግሞ ኢማምነት ተቋዊ ነው ይላሉ። ሁሉም ኢማሞች አልፈዋል። ከመጪው ኢማም ውጭ ሌሎች ኢማሞች መጥተዋል። የመጪው ኢማም ግን ተሰወረ እንጂ አልሞተም። ይህ ኢማም በመጪው ዘመን ከተሰወረበት በመውጣት በዓለም ላይ ፍትህ ያሰፍናል ብለው ያምኑ ነበር። በፋጢሚዮች ጊዜ አ.ሒ.አ በ408 ሐምዛ ኢብን ዓለ የተባለ ግለሰብ ሸሊፋው አምላክ ሁነዋል በማለት መናገሩን ተከትሎ፣ አክራሪ የሺዓ እና የኢስማዒሊያ ቡድኖች ሸሊፋ አል-ሐኪም ቢአምረላህን እንደ አምላክ መመልከት ጀምረው ነበር። በተጨማሪም ሐምዛ ኢብን ዓለ በዚህ ሳያቢቃ መፅሃፍ አሳትሞ ነበር። በመፅሃፉ ውስጥም የሸሊፋውን አምላክነት የሚያረጋግጥ ተረት እንዲህ በማለት ፈጥሮ ነበር፡- "(በመጀመሪያ) አምላክነት በአደም ውስጥ ሰርፆ ነበር፣ ከዚያም ወደ ዓለ ኢብን አቢ-ጧሊብ ተሳመረ፣ የዓለ ነፍስ ደግሞ ወደ አል-ዓዚዝ ተመለሰች፣ ቀጥላ ወደ ልጁ አል-ሐኪም ሔደች፣ አል-ሐኪምም አምላክ ሆነ።"

"አል-ባቢኒያ" በመባል የሚታወቁት ቡድኖች እምነትን የመሳሰሉ ልምምት ሃያመሪው በዚሁ ቤሐምባ ኢብን ዓሊ ነበር።

ሰላሉዲን የንብዕ የበላያ አስተዳዳሪ (መዚር) ሁኖ በሽሊፋው የተሾመ ጊዜ በያሩ አልተናገረውም እንጂ በልቡ ግን እነዚያን የትፕፈት ስብስቦች ሊታገላቸው ቆርጦ ነበር። የሃሰት ዕምነቶቻውን ነቃትሱ በመባል ቡትክክለኛ ኢስላማዊ ዕምነት (በስና) ሊተካቸው ለራሱ ቃል ገብቶ ነበር። ሳላሃዲን ግን ጅግና ብቻ ሳይሆን ብልህም ነበርና የልቡን በልቡ ያዙ ትክክለኛውን ጊዜ ይጠባበት ነበር። ከጥቂት ወራት በኋላ በመላ አገራቱ ትምህርት ቤቶችን ከፈተ። በተለይ አንዳሊሪያህ እና አል-ካሚሊያህ አሮጌ የገነኑ ትምህርት ቤቶች ነበሩ። ትልቁና ቀዳሚው ሥራ የስሙትን አዕምሮ እና ልብ መለወጥ መሆኑን ጠንቅቆ ያውት ነበርና ዕድሜ ላያገኛቸው ዜጎች ሁሉ ወደነዚህ ትምህርት ቤቶች ገብተው እንዲማሩ ትዕዛዝ አስተላለፈ። ዕውነተኛውን ኃይማኖት እንዲያጠኑ፣ ትክክለኛውን ኢስላም እንዲያውቁ፣ የነቢያን (የአላህ ሰላምና ዐጋ በእርሳቸው ላይ ይሁን) እና የሰሃቦቻቸውን ፈለግ እንዲከተሉና ካልደፈረሰው ምንጭ እንዲጠጡ የማድረግ ጥረቱን በትምህርት ጀመረ።

በማህበረሰቡ ውስጥ ሥር ሰደው የነበሩ ሃሰትዊ ዕምነቶችን ከሥራቸው ነቃትሱ ለመጣል፣ ከሁሉም በላይ ሳላሃዲንን የረዳው ግን በግብፃዊያን ዘንድ ያተረፈው ፍትር እና እምነት ነበር። ፍራንኮችን ደምሚታ ላይ ሲያሸንፋቸው፣ ጋዛ ላይ ሲደቁሳቸው እና ግብፃዊያንን ጨምሮ ለሌሎች ሙስሊም ሐዲጆች በሙሉ የቀይ ባህር በር የሆነችውን ዓቡባህን ከመዳፋቸው ሳንጠቃቸው ጊዜ ግብፃዊያኑ የበሌጠ እፈቀሩት። ይህ ትሉት ድል የሐዘ ተነሳችን ሰላም ከማረጋገጡ ጋር ተያምረው የህዝቡን ተሰብ ገዝተውለት ነበርና ከሺኅ ጦሙት አውጥቶ ወደ ስና ጎዳና የመለሰውን ሐኪት ሙላ ውረድ ያልበዛበት እደረጉት። ሀገሱ በተራው የእላህን ሰላቶች ለመታገል ኩላሃዲን ጎን ቆመ።

ላሬ በስና ጎዳና ላይ የሚመላለሱ ግብፃዊያን ከፍለው የማይዜልቱት የሰላሉዲን እዳ እና ውለታ እንዳለባቸው ሊያስታውሱ ይገባል።